# ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት  አመራር ኮሚሽን
# ብሔራዊ የጎርፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ መፅሄት ቁጥር-2

ሰኔ 01/2014ዓ.ም.



በሚያዚያ 2013 በሶማሌ ክልል በሸበሌ ዞን የደረሰ የጐርፍ ጉዳት

## መግቢያ

በበልግ እና በመኸር የዝናብ ወቅቶች ከዝናብ መብዛት እና ከአካባቢዉ የመሬቱ አቀማመጥ ጋር ተያይዞ ቅፅበታዊ ጐርፍ እና በወንዝ ሙላት ምክንያት የጐርፍ አደጋ ሊከሰት ስለሚችል አደጋዉን ቀድሞ ለመከላከል፣ ጉዳቱን ለመቀነስ እና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ለጐርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖረዉ ሕብረተሰቡ አስቀድሞ ተገቢዉን ጥንቃቄ እንዲያደርግ የጐርፍ አደጋ ስጋት መኖሩን ማሳወቅ፣ ግንዛቤ መፍጠር ወሳኝ ነዉ፡፡ በዚሁ መሠረት እ.ኤ.አ በ2022 የበልግ ወቅት አጋማሽ የአየር ትንበያ አዝማሚያን መሠረት በማድረግ በዝናብ ዕጥረትም ሆነ መብዛት ምክንያት ሊደርስ የሚችለዉን ጉዳት ጐርፍን ጨምሮ ለመከላከል እና ለመቀነስ ሊወሰድ የሚገባዉን ቅድመ ዝግጅት እና የመከላከል እርምጃ በተመለከተ ሊወሰድ የሚገባዉን እርምጃ ላይ ያተኮረ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መፅሄት ቁጥር 1 በሚያዚያ 05/2014ዓ.ም ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች መሰራጨቱ ይታወቃል፡፡

በዚህ የክረምት ወቀትም የዝናቡ ሁኔታ በአብዛኛው የአገሪቱ የምእራብ፤ የሰሜን ምእራብ የሰሜን፤ የሰሜን ምስራቅና የመካከለኛው የአገሪቱ ክፍል መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆን ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን የህም ሁኔታ በብዙ ቦታወች ላይ በከፍተኛ ዝናብና በወንዞች መሙላት ምክንያት የጎርፍ ክስተት ሊኖር ስለሚችል ተጎጂ ሊሆን የሚችሉትን የማህበረሰብ ክፍሎች ከሚደርስባቸው አደጋ ለመከላከል ይህን ቁጥር ሁለት የጎርፍ ማስጠንቀቂያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

### በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲቱት ለ2022 የክረምት ወቅት የተሰጠ ትንቢያ

በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲቱት ከተሰጠዉ የክረምት ወቅት የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ትንበያ መረዳት እንደተቻለዉ በበአብዛኛዉ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ አካባቢዎች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ነዉ፡፡

- በመሆኑምመደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ በሰሜኑ የአገራችን አጋማሽ  እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡
- በአገሪቱ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በማዕከላዊ እና በምስራቅ አካባቢ ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ ዝናብ የመኖር ዕድሉ ያመዝናል፡፡
- የደቡብ የአገሪቱ  ክፍል መደበኛና ከመደበኛዉ በታች ዝናብ  ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል ፡፡
- በአገረቱ በአብዛኛዉ የክረምቱ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ አካባቢዎች የክረምት ዝናብ አገባብ መደበኛ ፈሩን የተከተለ መሆኑን፣ አወጣጡ ግን የመዘግየት ሁኔታ እንደሚኖረዉ ትንበያዉ ያመለክታል ፡፡

# ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት አመራር ኮሚሽን
# ብሔራዊ የጎርፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ መፅሄት ቁጥር-2

## ሰኔ 01/2014ዓ.ም.

- በሐምሌና ነሐሴ ወር አልፎ አልፎ ከበድ ያለ ዝናብ እንደሚጠበቅ ለጐርፍ ተጋላጭ በሆኑ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ጐርፍ እና የመሬት መንሸራተት ሊያስከትል እንደሚችል ትንበያዉ ያመለክታል ።
- በሰኔ እና በመስከረም ወር የዝናብ ስርጭት የመዋዥቅ ባሕሪ ያለው እና የተወሰነ ረዘም ያለ ደረቅ ሰሞን እንደሚኖር ይጠበቃል።
- በጥቅሉ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ቦታዎች ላይ ርጥበት የበዛበት የክረምት ወቅት እንደሚኖር ተተንብዩዋል።
- ለ 2022 የክረምት ወቅት ተመሳሳይ የአየር ሁኔታ (best Analogue years) አላቸዉ ተብለዉ የተመረጡ አመታት እ.ኤ.አ 1985 እና 2000 ናቸዉ።
- በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲቱት ከተሰጠዉ የክረምት ወቅት የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ትንበያ ላይ የመጪው በጋ ዝናብ በደቡብና በደቡብምራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመደበኛ በታች እንደሚሆን ተጠቁሟል።

*2014 የክረምቱን የዝናብ ሁናታ የሚያሳይ ትንበያ*




ይህ የጐርፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ቁጥር 2 በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲቱት ለ2014 ዓ.ም. የክረምት ወቅት የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ትንበያን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነዉ፡፡ በክረምት ወቅት በመደበኛ ሁኔታ የጐርፍ ክስተት ሊያስከትል የሚችል ከፍተኛ የዝናብ መጠን የሚስተዋለው በሐምሌ እና በነሐሴ ወራት ሲሆን በተለይ ለጐርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች አልፎ አልፎ የጐርፍ ክስተትና በአንድ አንድ ቦታዎች ደግሞ የመሬት መንሸራተት ክስተት ሊያጋጥም ስለሚችል ከኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ የተሰጠዉን ማለትም እ.ኤ.አ የ2022 የክረምት የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ትንበያ ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት ለጐርፍ እና ለመሬት መንሸራተት አደጋ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን በመለየት ቅድመ ጥንቃቄ እንዲደረግ፣ የተሰጠዉንም ትንበያ በየክልሉ ለጐርፍ ተጋላጭ ለሆነዉ ህብረተሰብ በወቅቱ እንዲያዉቀዉ በማድረግ የጐርፍ ሆነ የመሬት መንሸራተት አደጋዉ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስቀደሞ ለመከላከል እና አደጋዉ የሚያደርሰዉን ጉዳት ለመቀነስ ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግ እና እንዲሁም ለአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ የሚወሰዱ እርምጃዎች ከወዲሁ የተመቻቹ እንዲሆኑ ለማድረግ መሆኑን እናሳስባለን፡፡ በቀጣይ በሚዘጋጀው የጐርፍ መጠባበቂያ ዕቅድ ላይ በዝርዝር የዝግጁነትና ጉዳቱን ለመቀነስ የሚያስችል ርምጃዎችን እንዲሁም የሚተገበሩ የምላሽ ስራዎች ይገለፃሉ፡፡

# ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት  አመራር ኮሚሽን
# ብሔራዊ የጎርፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ መፅሄት ቁጥር-2

ሰኔ 01/2014ዓ.ም.

## የጐርፍ አደጋ ስጋት ሊኖርባቸዉ ይችላል ተብለዉ የተለዩ ቦታዎች

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስትትዩት እ.ኤ.አ የ2022 የክረምት ወቅት የአየር ሁኔታ ትንቢያን እና የረጅም አመታት መረጃዎችን መሰረት በማድረግ እ.ኤ.አ በ2022 በክረምት ወቅት የጎርፍ አደጋ ስጋት ያለባቸውን አካባቢዎች በዝርዝር በየክልሉ በመለየት እንደሚከተለዉ ተሰርቷል፡፡

**በዘንድሮው የክረምት ዝናብ ትንብያመሰረት ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ የሚጠበቅባቸው አካባቢዎች በተለይ ትኩረት የሚሹ ማለትም አማራ (በጣና ተፋሰስ ስር ያሉ ወረዳዎች)፣ ትግራይ ( ደቡባዊ እና ደቡብ ምስራቅ)፣ አፋር (በአዋሽ ወንዝ ዳርቻ ያሉ አካባቢዎችና በሚሌ እና ሎግያ ወንዞች ወደ አዋሽ መዳረሻ የሚገኙ አካባቢዎች)፣ ድሬ ዳዋ ከተማ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ሰሜን ሶማሌ (ሽንሌና ፋፈን (ጅግጅጋ ከተማ) ዞኖች)፣ ኦሮሚያ ( በላይኛው አዋሽ ተፋሰስ ያሉ አካባቢዎች) እና ደ/ብ/ብ/ህ ክልል (ደቡብ ኦሞ ዞን) ናቸው፡፡**

**አማራ ክልል፡- ደቡብ ጎንደር ዞን-** ሊቦ ከመከም፣ ፎገራ እና ደራ ወረዳዎች፤ **ማዕከላዊ ጎንደር-** ደምቢያ፣ ጎንደር ዙሪያ፣ ምዕራብና ምስራቅ በለሳ፣**ምዕራብ ጎጃም-** ባህርዳር ዙሪያ እና ሰሜን አቸፈር ወረዳዎች፤ **ምሥራቅ ጎጃም፡-**አዉበል እና መቸከል ወረዳዎች፣ **ኦሮሞ ዞን-** ጂሌ ጡሙጋ፣ አርቱማ ፉርሲ፣ ከሚሴ እና ዳዋ ጨፋ  ወረዳዎች፤ **ሰሜን ሸዋ-** አንጾቂያ፣ አጣዬ ከተማ፣ ሸዋ ሮቢት፣ ቀወት፣ ኢፍራታ ግድም እና እንሳሮ ወረዳዎች፤ **ሰሜን ወሎ፡-** ቡግና፣ ወልደያ ከተማ፣ቆቦ፣ መርሳ ከተማ፣ **ደቡብ ወሎ-** አምባሰል፣ከምቦልቻ ከተማ፣ ደሴ ዙሪያ፣ ደሴ ከተማ፣ ሐይቅ ከተማ እና ቃሉ ከተማ፡፡ ከዚህም በተጨማር ከዚህ በፊት ጎርፍ ታይቶባቸው የማያውቁ ቦታወችም ክስተት ሊያስተናግዱ ስለሚችሉ የመከላከል ትግባራትን እንዲሰሩ ይመከራል፡፡

**አፋር ክልል፡- ዞን 1-** ዱበቲ፣ አሳይታ፣ ሚሌ፣ ጭፍራ እና አፋምቦ ወረዳዎች፤**ዞን 2-** አባአላ፣ በርሃሌ፣ መጋሌ እና ኮኔባ ወረዳዎች፣**ዞን 3-** አሚባራ፣ገላዕሎ፣ ገዋኔ፣አዋሽ ከተማ፣ ዱለቻ፣ ሀሩካ  እና አዋሽ ፈንታሌ ወረዳዎች፤ **ዞን 4-** ጉሊና፣ቴሩ፣ያሎ እና እዋ ወረዳዎች፣ **ዞን 5 -** ዳሊፈጌ፣አርጡማ፣ ዳዌ እናሰሙ ሮቢ ወረዳች፡፡

**ትግራይ ክልል፡-ምዕራባዊ ትግራይ-** ቃፍታ ሁምራ እና ፀገዴ ወረዳዎች፤ **ምሥራቅ ትግራይ** ሐዉዜን፣ **ሰሜን ምዕራብ ትግራይ፡-** ታህታይ ቀራሮ፣  **ደቡባዊ ትግራይ-** አላማጣ፣ ራያ አዘቦ፣ማይጨው ከተማ፣ ኦፍላ እና እንዳ መሆኒ ወረዳዎች፡፡ ከዚህም በተጨማር ከዚህ በፊት ጎርፍ ታይቶባቸው የማያውቁ ቦታወችም ክስተት ሊያስተናግዱ ስለሚችሉ የመከላከል ትግባራትን እንዲሰሩ ይመከራል፡፡

**ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፡- አሶሳ ዞን፡-** አሶሳ እና ሸርኮሌ ወረዳዎች፣ **መተክል ዞን፡-** ቡለን፣ ወንበራ እና **ፓዌ ልዩ ወረዳ**

**ጋምቤላ ክልል፡- ኑዌር ዞን-** ዋንታዋ፣ ላሬ፣ አኮቦ፣ ማኩወይ እና ጂካዎ ወረዳዎች፤ **አኝዋክ ዞን-** ጋምቤላ ዙሪያ፣ ጋምቤላ ከተማ፣ ዲማ፣ ጆር፣ ጎግ እና አቦቦ ወረዳዎች፤ **መጅንገር ዞን-** መንገሺ ወረዳ እና **ኢታንግ ልዩ ወረዳ**፡፡

**ኦሮሚያ ክልል፡-ምዕራብ ሀረርጌ ዞን-**ሃብሩ፣ሃዊጉዲና እና ኦዳ ቡለቱም ወረዳዎች፤ **ምስራቅ ሃረርጌ-** ጉሎኦዳ፣ ጉሮጉቱ፣ ጃርሶ፣ ጉርሱም፣ ደደር፣ ግራዋ፣ በደኖ እና ሜታ ወረዳዎች፤ **ምዕራብ አርሲ-** ሻላ፣ አርሲ ነገሌ፣ ሲራሮ፣ ኮፈሌ፣ ነንሰቦ እና ኮሬ ወረዳዎች፤**አርሲ፡** ዝዋይ፣ ጮሌ፣ ዱግዳ፣ ጎሎልቻ፣ ሮቤ፣ አሰኮ እና ሴሩ ወረዳዎች፤ **ባሌ-** አጋርፋ፣ ለገሂዳ፣ ጋሰራ፣ ጎሎልቻ፣ ጊኒር፣ ሴዌይና፣ በርበሬ እና ጉራዳሞሌ ወረዳዎች፤**ምዕራብ ወለጋ-** መንሰቦ፣ ጊምቢ፣ **ምዕራብ ሸዋ-** አቡነ ገንደበረት፣ ወልመራ፣ ደንዲ፣ ግንደበረት፣ ኤጀሬ፣ ጊንጪ፣ ሆለታ እና ኤጀርሳ ለፎ ወረዳ፤ **ደቡብ ምዕራብ ሸዋ-** ኢሉ፣ በቾ እና ዳዎ ወረዳዎች፤ **ምዕራብ ጉጂ፡-** ገላና፣ ቡሌ ሆራ እና አባያ፣ **ጉጂ-** አዶላ፣ ኡርጋ፣ ቦሬ፣ ሃናሶራ፣

ሰባቦሩ እና ዲማ ወረዳዎች፤ **ምስራቅ ሸዋ-** ቦሰት፣ ሊበን ጨቋላ፣ ቦራ፣ አዳማ ከተማ፣ አዳማ ወረዳ፣ አዳሚቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ፣ ፈንታሌ እና ሉሜ ወረዳዎች፤ **ሰሜን ሸዋ-** ያያ ጉለሌ ወረዳ እና ሰበታሀዋስ እና ሰበታ ከተማ፡፡ ከዚህም በተጨማር ከዚህ በፊት ጎርፍ ታይቶባቸው የማያውቁ ቦታወችም ክስተት ሊያስተናግዱ ስለሚችሉ የመከላከል ትግባራትን እንዲሰሩ ይመከራል፡፡

**ደ/ብ/ብ/ህ/ክ፡- ደቡብ ኦሞ ዞን-** ዳሰነች፣ በናፀመይ፣ጋንጋቶም፣ ሰሜን አሪ፣ ደቡብ አሪ፣ ኩራዝ፣ ሃምር እና ሰላማጎ ወረዳዎች፤ **ሃድያ-** ሻሸጎ፣ አኔሌሞ፣ ምሥራቅ በደዋቾ እና ምዕራብ ባደዋቾ ወረዳዎች፤ **ወላይታ-** ሁምቦ፣ ዳሞት ዋይዴ፣ ዱግዳ ፋንጎ፣ ኪንዶ ዲዳዬ፣ ኪንዶ ኮይሻ፣ ኦፋ፣ ሶዶ ዙሪያ፣ቦሎሶ ሶሬ እና ቦሎሶ ቦመቤ ወረዳዎች፤ **ሃላባ ልዩ ወረዳ-** ሃላባ ወረዳ፤ **የም ልዩ ወረዳ፣ ባስኬቶ ልዩ ወረዳ፣ አማሮ ልዩ ወረዳ፣  ከንባታ ጠባሮ፡-** አንጋጫ እና ቀዲዳ ጋሜላ፣ **ሰገን፡-** ኮንሶ እና ቡረጂ፣ **ጌዲዮ** ኮቸሬ፣ ቡሌ፣ ወናጎ እና ይርጋ ጨፌ፤ **ስልጤ-** ዳሎቻ፣ ላንፋሮ፣ሁልባረክ፣ ምስ/ሰልጢ ሳንኩራ እና ስልጤ ወረዳዎች፤ ዳዉሮ፡- ገና ቦሳ፣ **ጋሞ ዞን ፡-** ጨንቻ፣ ዲታ፣ ዳራማሎ፣ ቦንኬ፣ ምዕራብ አባያ፣ ከንባ፣ ቁጫ እና አርባምንጭ ዙሪያ፣ **ጎፋ ዞን፡-** ጊዜ ጎፋ፣ መለኮዛ፣ ኡባ ደብረፀሐይ እና ደምባ ጎፋ፣ **ጉራጌ-** ሶዶ፣ እነሞር፣መስቃን እና ማረቆ ወረዳዎች፡፡

**ሲዳማ ክልል-** ሎካ አባያ፣ ሃዋሳ ዙሪያ፣ቦሪቻ፣ ሃዋሳ ከተማ፣ ሽበዲኖ፣ ወንዶ ገነት እና ሁላ፤

**ሶማሌ ክልል፡- ሽበሌ ዞን-** ቀላፎ፣ ሙስታሂል፣ ፊርፊር፣ ጎዴ፣ በራኖ፣ ደናን፣ አዳዲሌ፣ አባኮሩ እና ምስራቅ ኢሚ ወረዳዎች፤ **አፍዴር-**  ምዕራብ ኢሚ፣  ጨረቲ እና ዶሎባይ  ወረዳዎች፤ **ሊበን-** ዶሎ ኦዶ እና በኮልማየ ወረዳ፤ **ቆረሄ፡-** ደበወይን **ፋፈን-** ጂግጂጋ፣ ጉርሱም እና ባቢሌ ወረዳዎች፤ **ጀራር፡-** ጉናጋዶ እና ቢርኮድ ወረዳዎች፣ **ሲቲ-** ኤረር እና ጋብላሉ ወረዳዎች፣ **ዳዋ-** ሙባረክ እና ሁደት ወረዳዎች፣ **ነጉብ -** ኤልዎየ ወረዳ፥ **ኤረር-** ለገሂዳ እና ቁቢ ወረዳዎች

**ድሬ ዳዋ ከተማ መስተዳድር፡-** ድሬ ዳዋ ከተማ (02፣03፣05፣06፣08 አና 09) እና የገጠር ቀበሌዎች (መጀ፣ ከረሶ፣ ጀሎ፣ አሳሊሶ፣ በዩአወሌ፣ በተሊሌ፣ ለገደል፣ መልሳቀሮ እና ኩላዩ)

**ሀረሪ ክልል፡-** ሀረር ከተማ

**አዲስ አባባ፡-** የጎርፍ ተጋላጭ ወረዳዎች

**ለመሬት መንሸራተት ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች**

**ኦሮሚያ ክልል፡  አርሲ፡-** አሰኮ፤  **ምዕራብ ጉጂ፡-** ገላና፣ ቡሌ ሆራ እና አባያ፣ **ሰሜን ሸዋ-** ወረጃርሶ፣ ጊቢቾ አና ደራ፣ **ምዕራብ ሸዋ፡-** አቡና፣ ግንደበረት፣ጀለዱ እና ሜታ ሮቤ፣ **ጂማ ዞን፡-** ጂማ፣ዴዶ፣ ጎማ፣ ሰቃ ጨቆርሳ፣ **ምስራቅ ወለጋ ዞን፡** ሣሲጋ ወረዳ፡፡

**አማራ ክልል፡- ምሥራቅ ጎጃም፡-** አወበል፣  **ሰሜን ሸዋ-** አንጾኪያ፣ባሶ እና ወረና፣ ጣርማ በር እና መርሀ ቤቴ ወረዳዎች፤ **ሰሜን ወሎ፡-** ሐበሩ እና መቄት፣ **ደቡብ ወሎ-**  ደሴ፣ መቅደላ፣ ሳይንት፣ወረባቦ እና ቃሉ  ወረዳዎች፡፡

**ደ/ብ/ብ/ህ/ክ፡- ደቡብ ኦሞ ዞን-** ደቡብ አሪ እና ሃምር፣ **ሃድያ-** ሻሸጎ  እና ሶሮ ወረዳዎች፤ **ወላይታ-** ቦሎሶ ሶሬ፣ ኦፋ፣ ዳሞት ሶሬ እና ቦሎሶ ቦመቤ ወረዳዎች፤ **ከንባታ ጠባሮ፡-** ቃጫ ቢራ፣ **ሰገን፡-** ኮንሶ እና ቡረጂ፣ **ጌዲዮ**  ቡሌ እና ወናጎ፤ **ዳዉሮ፡-** ሎማ፣**ጋሞ ዞን ፡-** ጨንቻ፣ ዲታ፣  ቦንኬ፣ ምዕራብ ጋርዱላ፣ ከንባ፣ ቁጫ፣ **አማሮ ልዩ ወረዳ፣ ጎፋ ዞን፡-** መለኮዛ፣ ዑባደበረፀሐይ፣ ደንባ ጎፋ እና ጊዜ ጎፋ፣ ቀረጫ እና አርባምንጭ ዙሪያ፣ **ከፋ ዞን፡-** ዲቻ፣ ዲታ፣ ጨታ እና ጊንቦ፣ **ጉራጌ-** ሶዶ፣ መስቃን፣ ማረቆ፣ ምሁር እና አክሊል ወረዳዎች፡፡

## ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት  አመራር ኮሚሽን
## ብሔራዊ የጎርፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ መፅሄት ቁጥር-2

ሰኔ 01/2014ዓ.ም.

**ሲዳማ ክልል-** ዳሌ፣ ሎካ አባያ፣ ሃዋሳ ዙሪያ፣ ሸበዲኖ፣ ወኔሾ እና ሁላ፤

**ትግራይ ክልል፡-** መአከላዊ ትግራይ ዞን፡- ቆላ ተንቤን አና አክሱም

<u>የቅድመ ዝግጅትና ጐርፍን አስቀድሞ ከመከላከል አንጻር በቅድሚያ ሊሰሩ የሚገቡ ስራዎች፡-</u>

- ለጎርፍ ስጋት ተጋላጭ የሆነዉን ማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ ተደራሽ ማድረግ፣
- በብሔራዊ የጐርፍ ግብረሃልና በክልሎች ግብረሃይል መሃል ተከታታይነት ያለው መረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ፡
- በጐርፍና የመሬት መንሸራተት ስጋት ውስጥ ያሉትን አካባቢዎች በተመለከተ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን በወቅቱ ለህብረተሰቡ ማሰራጨት፣
- የጐርፍ መከላከያ መዋቅሮችን ማጠናከር፣
- ማህብረሰቡ ላይ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ንቁ ሆኖ እንዲጠብቅ ግንዛቤ መፍጠር፣
- በተዳፋት ቦታዎች የጎርፍ ፍሰት ፍጥነትን ቀድሞ ለማወቅ እንዲቻልና ለሚወሰደው እርምጃ ዝግጅት ለማድረግ በደጋማ ቦታዎች እና በዝቅተኛ አካባቢዎች ባለው ማህበረሰብ መካከል ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ፣
- የጐርፍ አደጋው የሚፈጠርበት ሁኔታዎች/ምልክቶች ከታዩ ማህበረሰቡን በፍጥነት ወደ ከፍተኛ ቦታ ለማንቀሳቀስ እና የአስቸኳ ጊዜ ድጋፍ ማቅረብ የሚያስችል አሰራር ታሳቢ ማድርግ፡፡
- በወቅቱ ተደራሽ ለመሆን በንቃትና በቅርበት የስጋት አካባቢዎችን ክትትል ማድረግ፡
- የማስጠንቀቅያ፣ የዝግጅት ስራዎችንና አደጋውን ለማቅለል የሚወስዱ ተግባራትን በየደረጃዉ ማከናወን፣
- ለጎርፍ መውረጃ የሚያገለግሉ ቦዮችን ማጽዳትና አዲስ መዘጋጀት ያለበት ቦታ ላይማ የማዘጋጀት ስራ መስራት፤

የወንዞችን የውሃ ከፍታ መጠን መከታተል፣ለሚመለከተዉ አካል በወቅቱ ሪፖረት ማድረግ፡

- የክልሎችንና የዞኖችን የጐርፍ ግብረሃይል ድጋፍ ማድረግ፣ እንደገና ማንቀሳቀስና ማጠናከር፡
- የዳሰሳ ጥናት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ዘርፈ ብዙ ኤጀንሲዎችንና ሴክተሮችን ማሳተፍ፡
- ከቀበሌ መዋቅር እስከ የብሔራዊ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የቅንጅት ስራዎችንና የመረጃ ልውውጥን ማጠናከር፡
- ለመስኖ ስራ የተከፈቱ የውሃ ማስወጫ ቦየችን መዝጋትና አፈር በመጠቅጠቅ ማጠናከር፤
- የዝግጅት እና የመከላከል ተግባራት (ውሃ ማቆር፣ የዉሃ መዉረጃ ቦዮችን መጥረግ፣ ወንዞች ውሃ ሰብሮ የሚወጣበትን አካባቢ ማጠናከር) ሥራዎችን ማበረታታት፣
- ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ማሻሻል፣ ውሃን ማከም፣ ንጽህናን ለመጠበቅና በሽታን ለመከላከል የሚወሰዱ ርምጃዎች ማጐልበት፣ እንደ አጣዳፊ ተውከትና ተቅማጥ የመሳሰሉትን ተላላፊ በሽታዎችን በቅርብ መከታተልና መከላከል፣ ሌሎች ከጤና ጋር የተያያዙ የስነምግብና ጤና ነክ

የሆኑ ስራዎችን በመስራት በጎርፍ ምክንያት በህይወትና በንብረት ላይ የሚደርሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ መቀነስ፡

- የተቀናጀ ዘርፈ ብዙ ሴክቶራል የጐርፍ መጠባበቂያ እና ምላሽ እቅድ እንደአስፈላጊነቱ ማዘጋጀት እና በተለይ ለአደጋው ምላሽ መስጠት የሚያስችል ግብ ያደረገ ስራን ማከናወን፡

- የቅፅፈታዊ ጐርፍና የወንዝ ሙላት የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለመቀነስ፡- የጐርፍ ማፋሰሻ ግንባት እና ለጐርፍ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የጐርፍ መከላከያ ሥራዎችን እንዲሁም ተሳትፎና ግንዛቤን በማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመስራት የጐርፍ መከላከያ ሥራዎችን ማጠናከር እና ሌላም አስፈላጊ የሆኑ የመከላከያ ፋሲሊቲዎችን ማሻሻል፡

- በአጋባቢው የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር የኃብት ማሰባሰብና በጎርፍ ቅድመ መከላከል ትግባር እንዲሰሩ ማስቻል፡፡ እንዲሁም በመጠባበቂያ እቅድ ዝግጀትና የሃብት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ማድረግ፤

- ጐርፍን ለመከላከል በሚሰሩ በሁሉም ተግባራት ውስጥ የማህብረሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡